# ድንቄም ተቃዋሚ

በ ዲነካ ኮርንማ
ዋሽንግተን ዲሲ

ኸረ ለመሆኑ ይኸ ፖለቲካ- በምድረ አሜሪካ
መላቅጡ አጣሁት አልገባኝም ለካ!
እኔ ማውቀው? የጥንቱ? የሰለጠኑቱ?
የአስተሳሰብ ልዩነት ቢኖር እንኳ በመሰረቱ
ልዩነቴ የግል - ሀገር ግን የጋራ ብለው የሚሞቱ፤
ግን ይኸ አይደለም በጥቂቶች 'ማየው
መላቅጡ የጠፋ ወለፈንዴያዊ ነው።
ኣካካካካ ............. ድንቄም ተቃዋሚ
አገርን ለመጉዳት ከጠላት ተስማሚ!
የነጻነት ታጋይ መስሎ በመታየት
በጭፍን ጥላቻ ዲስኩርን በመንዛት
ጸረ-ኢትዮጵያ ሆነው ቀን ተሌት መኳተት?
ወቸ ጉድ! አለ ያገሬ ገበሬ
በጣም አስገረመኝ የሰሞኑን ወሬ።
ለሰላማዊ ሰልፍ አሎ-.... አሎ..... አሉና
ምንድነው ሲባሉ ድጋፍ ለሻዕቢያ እንዲሁም ለእንትና
መንገድና ድልድይ እንዳይሰራ አሉና
ታሪካዊ ስህተት ሰሩ እንደገና።
ቻይና የስራ ሰው ሰምቶ ዲስኩራቸው
የኢትዮጵያን ካባ ለብሰው በላያቸው
ያገራቸውን ልማት በመጻረራቸው
በጣም ተገረሙ ባፈጣጠራቸው።
የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ሆነና ነገሩ
ልጆቿ እያለሙ፣ እነኛ ጽንፈኞች ግን ለጥፋት መከሩ።
ኣካካካካ ............. ድንቄም ተቃዋሚ
አገርን ለመጉዳት ከጠላት ተስማሚ!
ምክሬን ይድረስህ ለንጹሁ ወገኔ
ሚስጥሩ ላልገባህ ለተሰለፍከው ያኔ
አስተባባሪዎቹ? አላማ አላቸው
ወርቅ እንኳ ቢነጠፍ ምንም አይጥማቸው።
ልማታችን እንዲቆም ሌት ቀን 'ሚጥሩ
የጭቃ እሾህ ሄነው የሚያናቁሩ

የግላቸውን ጥቅም በደምብ 'ሚያስከብሩ

"የቁርጥ ቀን ልጅ ነኝ!" እያሉ በዘመናዊ ልመና እየተሰማሩ

እንዲሁም ከጠላት ድጎማ የሚቹሩ

ልጆቻችን ናቸው.....................................

ለክፋም ለደጉም ጠንቅቀህ እወቃቸው

ይብላኝ ለእነሱ እንጂ ...............................

ኢትዮጵያ እንኳ እንደሆን አይቀርም ማደጓ

ልጆቿ እየለፉ ክረምት እና በጋ

ኣካካካካካ .............. ድንቄም ተቃዋሚ

አገርን ለመጉዳት ከጠላት ተስማሚ!

~ ፡፡ ~